# ከሥርዓተ አገዛዙ ጋር የተመሳጠሩ አውሮፓውያን ተልዕኮ ሕዝቡን እያነጋገረ እንደሚገኝ ተገለጠ

ሕዝብ እንዳያውቀው በከፍተኛ ጥንቃቄ ከሥርዓተ-አገዛዙ ጋር ተመሳጥረው ሐምሌ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በሔሊኮፕተር በጣና ደሴት በክብራን ገብርኤል ገዳም አጠገብ አርፈው የተመለሱ አውሮፓውያን ተልዕኮ ምሥጢር ሆኖ መቆየት እስካሁን ሕዝቡን እያነጋገረ እንደሚገኝ ስሞኑን አንዳንድ የጎንደር ከተማ ነዋሪዎች ገለጡ።

እንደ ነዋሪዎቹ አገላለጽ አውሮፓውያኑ የስዊዘርላንድ ተወላጆች ሲሆኑ ከጣና ደሴት ተነስተው በዚያው ቀን በላሊበላ ቅዱስ ሥፍራዎች ቆይታ ካደረጉ በኋላ በፍጥነት ወደ አዲስ አበባ መመለሳቸው ታውቋል።

ሚስተር ሉጂ እንዲሁም እንድሪያስ የተባሉትን ግለሰቦች ያካተተውና አራት አባላት የሚገኙበት ይህ የአውሮፓውያን ቡድን ወደ ደሴቲቱ መምጣቱን የገዳሙ ኃላፊዎች እንኳን እንዳያውቁ ተደርጎ ተልዕኳቸውን ፈጽመው በመጡበት ሔሊኮፕተር ባስቸኳይ የተመለሱበትን ምሥጢር ጊዜ የሚያወጣው መሆኑን የተናገሩት የጎንደር ነዋሪዎች ምናልባት ተልዕኳቸው ከቅርስ ምዝበራ ጋር የተያያዘ ሳይሆን እንደማይቀር ገምተዋል።

" ፈረንጆች በኢትዮጵያ ወሰን አግራቸውን ታጥበው እንዲወጡ ያዘዙት ጀግናው አጼ ቴዎድሮስ የተወለዱባት ጎንደር ዛሬ ኃላፊነት ከጎደላቸው ከሐዲዎች መዳፍ ሥር አሣሯን እየበላች ናት!" ያሉት ታዛቢዎች አስተያየታቸውን ሲደመድሙ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ቀድሞ ሁሉ አንድነቱን አጠናክሮ ቁሳዊና መንፈሳዊ የታሪክ ቅርሱን በመጠበቅ እንዲት ኢትዮጵያን ለመጭው ትውልድ ለማውረስ ቆርጦ መነሳት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

EthioLion.Com